የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ-ግንቦት ፬ ቀን ፳፻

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 30
ADDIS ABABA-12th May, 2008


## ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፻፶፩/፳፻
የአባይ ተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት እና ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት
ደንብ ...................................................... ገጽ ፬ሺ፹፮


## CONTENTS


Regulation No. 151/2008
Council of Ministers Regulation to Establish Abbay Basin High Council and Authority
................................................................ Page 4086


### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፶፩/፳፻ ዓ.ም የአባይ ተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት እና ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እንዲሁም በተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፬/፲፱፻፺፱ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአባይ ተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት እና ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፶፩/፳፻" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>መቋቋም</u>

፩. የአባይ ተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት እና ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪. ባለሥልጣኑ በተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፬/፲፱፻፺፱ መሠረት ይተዳደራል።

፫. <u>ዓላማ</u>

የባለሥልጣኑ አጠቃላይ ዓላማ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት ፍትሃዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ በዓባይ ተፋሰስ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ማበረታታትና መቆጣጠር ነው።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO.151 /2008 COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ABBAY BASIN HIGH COUNCIL AND AUTHORITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 21 of River Basin Councils and Authorities Proclamation No. 534/2007.

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Abbay Basin High Council and Authority Establishment Regulation No.151/2008".

2. *Establishment*

1. The Abbay Basin High Council and Authority (hereinafter the "Authority") is hereby established as an autonomous public organ having its own legal personality.
2. The Authority shall be governed by the River Basin Councils and Authorities Proclamation No. 534/2007.

3. *Objective*

The overall objective of the Authority shall be to promote and monitor the implementation of integrated water resources management process in an equitable and participatory manner in the Abbay basin.


ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.80

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O. Box 80,001

፬. <u>የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በባህርዳር ከተማ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በተፋሰሱ ውስጥ በንዑስ ተፋሰስ ደረጃ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. <u>የባለሥልጣኑ ከፍተኛ ምክር ቤት አባላት</u>

፩. የባለስልጣኑ ከፍተኛ ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ይሰየማሉ፡፡

፪. የባለሥልጣኑ ከፍተኛ ምክር ተጠሪነት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡

፮. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ሃሣቦችን በማመንጨት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

፪. በተፋሰሱ ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ለማስፈፀም የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

፫. በተፋሰሱ ውስጥ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶች ፣ ተግባሮችና መስተጋብሮች በይዘታቸው፣ በጊዜ ሠሌዳቸው፣ በውጤታቸውና በአመራራቸው ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

፬. የተፋሰስ ዕቅድ በማዘጋጀት ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

፭. ለክልሎች በሕግ የተሰጠ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተፋሰሱ ውስጥ በውሃ ለመጠቀምና ውሃ ነክ ሥራዎች ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ በተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤቶችና ባለሥልጣናት አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፬/፲፱፻፺፱ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ይሰጣል፣ በፈቃዱ የተመለከቱ ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣

፮. በተፋሰሱ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል ፣ ያሠራጫል፣

፯. የተፋሰሱን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ ዕቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፣ ይጠቀማል፣

፰. የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን ስለሚመለከቱ አለመግባባቶች አፈታት ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤትና ለውሃ ሀብት ሚኒስቴር የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

፱. አግባብ ባላቸው አካላት መካከል ውጤታማ የግንኙነት መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

4. *Head Office*

The Authority shall have its Head Office in Bahirdar and may have sub-basin branch offices in the basin as may be necessary.

5. *Members of the High Council*

1. The members of the High Council shall be designated by the Government.
2. The High Council shall be accountable to the Council of Ministers.

6. *Powers and Duties of the Authority*

The Authority shall have the following powers and duties:-

1. Initiate and submit to the Basin High Council policy measures needed to create a conducive environment for the the implementation of an integrated water resource management process within the basin; and follow up the implementation of the policy upon approval;
2. Undertake activities necessary for, and facilitate, the implementation of integrated water resources management in the basin;
3. Ensure that projects, activities and interventions related to water in the basin are, in their content, schedule, impacts and management are in line with the integrated water resources management process;
4. Prepare, and submit to the Basin High Council, the basin's plan and monitor its implementation upon approval;
5. Without prejudice to the power given to Regional States by law, issue permits applicable to the basin's water use and water works in accordance with Article 15 of the River Basin Councils and Authorities Proclamation No. 534/2007 and ensure that the terms of the permits are complied with;
6. Collect, compile, analyze and disseminate information for proper planning, administration and steering of water resources in the basin;
7. Develop and use a river basin model in order to guide and support its basin water resources strategic planning and water administration functions;
8. Give advice and technical support to the Basin High Council and the Ministry of Water Resources on dispute resolution in relation to the allocation and use of water resources of the basin;
9. Set up a forum for effective networking among stakeholders;

፲. ከተጠቃሚዎች የውሃ ክፍያ ይሰበስባል ፣

፲፩. ከሌሎች አገሮች ጋር ድንበር ዘለል ወንዞችን በሚመለከት ለመወያየት አግባብ ላለው አካል በተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት መመሪያ መሠረት አስፈላጊ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ይሰጣል፣

፲፪. ተግባሮቹን ለማከናወን የሚረዱ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችንና ምርምሮችን ያካሂዳል፣

፲፫. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል ፣ ይከሰሳል፣

፲፬. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፯. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ - ግንቦት ፬ ቀን ፪ሺ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

10. Collect water charges from users;

11. On the basis of instructions of the Basin High Council, prepare and provide necessary information for the concerned body in charge of negotiations with other countries concerning trans-boundary river basins;

12. Undertake studies, surveys and researches that are deemed necessary to carry out its functions;

13. Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

14. Carry out other functions necessary for the implementation of its objectives.

7. *Effective Date*

This Regulation shall come into force upon the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 12th day of May 2008.

**Meles Zenawi**

**Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**